"ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ?ተነስቶአል እንጂ በዚህ የለም።" ሉቃስ፤ምዕ24ቁ5-6

## ትንሣኤ

የመቃብሩን ድንጋይ ፈንቅሎ
የመግነዝ ጨርቁን አውልቆ ጥሎ
በአይሁድ ወታደሮች ላይ
በኃይል ሰልጥኖ
ክርስቶስ ተነሳ ከፍ ከፍ ብሎ።
ለማያልፍ ርስት ዳግመኛ የወለደን
ሕይወቱን ሰጥቶ ያከበረን
ለአዳም ልጆች ሁሉ ተስፋ የሆነን
ይኸው በኩራት ተነስቶአል ደስ ይበለን።
ከእንግዲህ ቀረልን በሞት መጠቃቱ
ሲፈርስ አይተነዋል የዲያብሎስ ግዛቱ
ክርስቶስ ሲነሳ በግርማ መለኮቱ።
እኛን በገዛ ደሙ ገዝቶ
በፍቅሩ ወድዶ ስቦ
ወደሚደነቅ ብርሃን ጠርቶ
ኃጢአታችንን ሽሮ አጥፍቶ
ዛሬ አየነው በክብር ተነስቶ
የእሱ የሆነውን በዲያብሎስ ላይ ሹሞ
ረግጠን እንድንገዛው ማህተሙን አትሞ
ትንሣኤ ሆነልን በጸጋው ሸልሞ።
አማኑኤል የተባለው
አልፋና ኦሜጋ የሆነው
መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው
እርሱ እኮ ራሱ ትንሣኤ ነው።
አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛ
ከበረዶ ይልቅ እጅግ የነጣ
ነጭ ልብስ ለብሶ ሲነሳ
ሞት ሆይ መውጊያህ ታዲያ የቱ ነው?
አዳምን ከክብሩ አውርዶ የለየው
ወደ መሬት ቁልቁል የጣለው
እኛስ ይኸው ዕልል ብለናል
ዳግማዊው አዳም ሲነሣ አይተናል
ዲያብሎስ እንደማይችለው አውቀናል።

29/03/04 ዓ/ም